# *ዘመነ ዴሞክራሲ፣ የነጻ አውጪዎችና የአምባገነኖች ፍጻሜ፣ ቅንጅት ቅንጀት በአለም ዙሪያ ባለፉት ሁለት አመታት፤*

*ከቀድሞው የአለም አቀፍ አመራር የድርጅት ጉዳይ ሃላፊ፣ አንዳርጋቸው ጽጌ*

*ማስታወሻ*
ይህንን ጽሁፍ፣ የቅንጅትን አለም አቀፍ አመራር የስራ ዘመን ፍጻሜ በሚመለከት የዲሲ ሜትሮ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት ከነጻነት ለኢትዮጵያ፣ ከአዲስ ሬዲዮ፣ ከሲቪክ ማህበራትና ከኢትዮጵያን ሪቪው ጋር በመሆን፣ ባዘጋጀው በአል ላይ ተናጋሪ እንድሆን በመጋበዜ በእለቱ በንባብና በገለጻ ለማቅረብ ያዘጋጀሁት ነበር። በግዜ መጣበብ ሙሉ ለሙሉ ለማቅረብ ባልችልም ለታዳሚው የተወሰነውን የጽሁፌን ጭብጥ ለማስተላፍ ሞክሬአለሁ። በስብሰባው የተካፈሉና በስብሰባው ያልነበሩ ወገኖቼ፣ ጸሁፉ ሰፊ አንባቢ ቢያገኝ ጥሩ ነው በማለት ስለመከሩኝ በንግግር መልክ እንዲቀርብ የተዘጋጀውን ጽሁፍ ለማስተካከል ግዜ ከማጥፋት ወቅቱ ሳያልፍ በስፋት ማሰራጨት ለሚችሉት የሚድያ አውታሮች ሁሉ ልኬዋለሁ። በበኩሌም አሁን ላለንበት ሁኔታ ይህ ጽሁፍ በጎ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ።

**ዋሽንግተን ዲሲ ኦገስት 18፣ 2007**

በቅድሚያ ይህንን አጋጣሚ ለፈጠራችሁት የዲሲ ሜትሮ ቅንጅት የድጋፍ ድርጅት አባላት የፕሮግራሙ አዘጋጆችና የፕሮግራሙ ታዳሚዎች የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ይህ ምስጋናዬ የመጀመሪያዬ እንጂ የመጨረሻው አይደለም። ወደ ንግግሬ መደምደሚያ፣ ከተሰጠኝ ግዜ የተወሰነውን በመጠቀም ምስጋና ለማቅረብ የምጠቀምበት ይሆናል።

የዛሬው እለት ፕሮግራም በበአል ስሜት የተዘጋጀ ነው። አላማውም ምስጋና የማቅረብ ቀለል ያለ ነገር ነው። በመሆኑም ብዙዎች ተናጋሪዎች በእዚህ ዙሪያ እንደሚናገሩ ይገባኛል። እኔ ግን ምንም ከቀኑ የበአል መንፈስ ጋር ባይሄድም የተሰጠኝን እድል በደረቅና ግትር በሆኑ ነጥቦች ላይ በማተኮር ልጠቀምበት ወስኛለሁ። በኔ እምነት በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ፣ ነጻነትና ፍትህ ለማስፈን የተጀመረው ትግል ተጀመረ እንጂ አላለቀም። ያለፉት ሁለት አመታት ያሳዩን ነገር ቢኖር ከመጨረሻው የድል ምእራፍ ለመድረስ ማለቂያ የሌላቸው ፈተናዎች ማለፍ እንዳለብን ነው። ይህ ፈተና በወያኔና ወያኔን በመሳሰሉ ድርጅቶች ብቻ የሚቀመር ሳይሆን እንደ ቅንጅት ተመሳሳይ የሆነ አላማ አለን ከሚሉ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችና ግለሰቦች ጭምር የሚወረወርብን ነው። ከሁሉ በላይ ግን ትልቁ ፈተና በራሳችን በቅንጅት ቤት ውስጥ ከተሰባሰቡ ቡድኖችና ግለሰቦች የሚነሳው ይሆናል። ከምርጫው ቀደም ባሉት ወራትና ከእዛም በኋላ በነበሩት ሁለት አመታት ግዜየን ያጠፋሁት በድርጅት ጉዳይ ዙሪያ በመሆኑ ይህ ፈተና ቅንጅትን እየገጠመው ያለው ቁልፍ በሆነው የድርጅት ጉዳይ ዙሪያ በመሆኑ በእዚሁ ላይ አተኩራለሁ። ፈተናው የአመለካከትና የድርጊት ፈተና ነው። የተሠጠኝን ግዜ ግምት ውስጥ በማስገባት ንግግሬን በተለያዩ አርእስቶች በመከፋፈል አቀርባለሁ።

*ሀ) በቅንጅት ዙሪያ የመደረጃት አላማውና ግቡ ምንድነው፡፡*

*ለምንድነው ከስራ፣ ከቤተሰብ ከመዝናኛ ግዚያችን፣ ከራሳችንና ከቤተሰባችን ጉርስ ገንዘባችንን እየቀነስን እውቀትና ጉልበታችንን እየተጠቀምን ቅንጅትን ለመደገፍ ተደራጅተን የምንማስነው፡፡ ለእዚህ ጥያቄ የሚያረካ መልስ መስጠት ካልቻልን የአላማ ጽናት አይኖረንም፡፡ ውለን አድረንም ድርጅታቸንን ቅንጅትን በሃገራችን እስካሁን ስልጣን ይዘው ህዝብን ካሰቃዩት የፖለቲካ ድርጅቶች የተለየ ማድረግ አንችልም፡፡ ደግነቱ ለእዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት በቅንጅት ውስጥ ከተጀመረ ውሎ አድሯል፡፡*

*ራስን፣ የሃገርና የወገን መከራና ስቃይ ተካፋይ ሳያደርጉ፣ ትግሉ የፈረደበትን ሃገርና ህዝብ ነጻ ለማውጣት ነው የሚለው የነጻ አውጪው አባባል በቅንጅት መሪዎች ሲተች ከርሟል፡፡ በኑሯቸው የተደላደሉ በእውቀታቸው አንቱ የታባሉና በሃብት የከበሩ የቅንጅት መሪዎች ሳይቀሩ ትግላቸው ለራሳቸው ነጻነትና ለራሳቸው መብት መከበር እንደሆነ በመናገር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለጋራ ነጻነቱና መብቱን ለማስከበር አብሯቸው እንዲቆም ጥሪ ማስተላለፍ ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡ እኔ ሀብትና ንብረት አለኝ ደልቶኝ እኖራለሁ የምታገለው ላንተ ነጻነት እና ጥቅም ነው የሚለው የቀድሞዎቹ ነጻ አውጭዎች ተረት በቅንጅት ውስጥ ቦታ ካጣ ውሎ አድሯል፡፡ የቅንጅት መሪዎችን መታሰር መንገላታት ምክንያት በማድረግ « እነዚህ ሰዎች ምን ጎሎባቸው ይመስልሃል ለህዝብ ብለው ነው የሚሰቃዩት» የሚሉትን ግለሰቦች አባባል መሪዎቻችን ምን ይህል እንደሚኮንኑት እናውቃለን፡፡*

*በተለያዩ ግዚያት ለምን እየአንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለዴሞክራሲና ለነጻነት ለፍትህ ለእኩልነትና ለአንድነት መታግል እንደሚገባው የቅንጅት መሪዎች ከሰጧቸው አጥጋቢ ምክንያቶች መሃል ጥቂቶቹን ልጥቀስ፡፡*

- *የቀደምቶቻችን የታሪክ አደራ፤ ይህ የታሪክ አደራ ካለንበት ወቅት በባሱ ተከታታይ ከሆኑ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ጋር በመጋፈጥ፣ ቀደምቶቻችን አይታለፉ ፈተናዎች በድል አልፈው ያቆዩትን ሃገርና ለበታኞችና ነጻነታችንና መብታችንን ከውስጥና ከውጭ ለሚጋፉ ሃገራዊና ህዝባዊ ክብራችንን ለሚያዋርዱ ሃይሎች ማስረከብ የለብንም የሚል እምነት ነው፡፡*
- *ለራሳችን የሚመች፣ ለልጆቻችን ብናወርሰው ሊኮሩበት የሚገባ፣ የሀገሪቱ ዜጎች መብት የተከበረበት፣ ፍትህ የሰፈነበት፣ ድህነትና በሽታ የተወገዱበት ሃገር የመገንባት ጉዳይ ነው፡፡*
- *በታሪካችን ውጣ ውረድ፣ በድልና በፈተናው፣ ለነጻነታችን በጋራ በተከፈለው መስዋአትነት፣ በጋራ ለተሳሰርነው ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የምትመች ሃገር የመገንባት ጉዳይ ነው፡፡*
- *ብዙሃኑ ያላገኙትን የመማር እድል ላላገኘ፣ በተለይ በኢትዮጵያ ገጠሮች ተቆራምዶ በሚኖረው የቅርብና የሩቅ ዘመዳችን ከእዛም ውጭ ባለው ኢትዮጵያዊ ወገናችን በተከፈለወ ታክስ የተማርነው ሁሉ ለህዝብ ውለታችንን የምንከፈልበት፤ ልጆቹ እኛ ያገኘነውን እድል እንዲያገኙ ብልጽግናና ሰብአዊ ደህንነት የሰፈነበት ሃገር መገንባት ነው፡፡*
- *ግፍና አሰቃቂ ድህነት እንዲወገድ በድህነትና በግፍ ላይ የማመመጽ ሰብአዊ ሞራላዊና ሃይማኖታዊ ግዴታ ስላለብን ነው፡፡*
- *የእውነተኛ ደስታ ምንጭ በመሆኑ ነው፡፡ በተለያዩ ክሮች ማለትም በዜግነት፣ በመወለድ፣ በባህል፣ በቋንቋ በእምነትና በሌሎችም ጉዳዮች ከሃገራችንና ከወገኖቻቻችን ጋር በመተሳሰራችን፤ በሃገራችን በተደጋጋሚ በሚከሰተው ረሃብ ወገናችንን እንደክረምት ጎመን በሚቀረድዱት ብዙ-ፈጅ በሽታዎች በእብሪተኛ ገዥዎች በየዘመኑ በሚፈሰው የንጹሃን ወገኖቻቸችን ደም መሳቀቃችን ማፈራችን አልቀረም፡፡ ከእዚህ እውነታ ጋር ተሳስሮ የሚመጣውን ግለሰባዊና የጋራ ሃፍረትና ውርደት ለማስቆም ነው፡፡ በገንዘባችን በእውቀታችን በግዚያችን በጉልበታችን፣ ዘለቄታዊነት ያለውን የብዙሃኑን ደስታ መሸመት ከቻልን*

የሚሰማን ሰብአዊ እርካታና ክብር ከየትኛውም አይነት ደስታ በጥልቀቱ እና በጥራቱ የላቀ ነው ብለን ስለምናስብ ብቻ ነው።

- ቅንጅት በሚመራው ትግል ውስጥ በመሳተፍ ባለፉት ሁለት አመታት በተደረገው ትግልና በተከፈለው መስዋእትነት፣ እንዲሁም ወደፊት በሚደረገው ትግልና መስዋእትነት የራሳችንንና የሃገራችንን ህዝብ ለዘመናት ሲሻው የኖረውን የነጻነት የብልጽግና የመብት መከበር ፍላጎት ያሳካን ትውልድ ሆነን ብንገኝ ሊሰማን የሚችለውን ታላቅ ደስታ ሰብአዊ ክብርና ኩራት መገመት ትችላላችሁ። አዲሱ የኢትዮጵያውያን የነጻነት የዴሞክራሲ የብልጽግና የታሪክ ምእራፍ ሲከፈት እኔም የድርሻየን አበርክቻለሁ ማለት መቻል ታላቅ ጸጋ እንደሆነ እናውቃለን። ከግብዝነት የራቀ ፍጹምና ንጹህ የሆነ ሰብአዊ ኩራት እንደሚያጎናጽፈንም እናውቃለን። ይህ እራሱን የቻለ የመታገያ ምክንያት ነው። እስካሁን እንደታየው ደግሞ በቅንጅት ዙሪያ የተሰባሰብነው ይህንን ማድረግ የሚያቅተን አይሆንም።

## ለ) እስካሁን ሃገርን ለማሻሻል ሲባል ስለተደረጉ ሙከራዎች በጥቅሉ

- ሃገርን የማሻሻል አላማ ለማሳካት በተለያየ ዘመን የተለያዩ ግለሰቦች እና ቡድኖች የተለያዩ ሙከራዎች አድርገዋል። ነገስታቱ፤ መሳፍንቱ፤ የወታደራዊና የሲቪል ልሂቃኑ፣ ጀነራሎቹ፣ ዝቅተኛ የጦር መኮንኖቹ፣ ተማሪውና ምሁሩ፤ በመሰላቸው መንገድ፣ የኖሩበት ዘመን ባላበሳቸው የእውቀት መጠን፣ የባህል እድገት፣ በፈቀደላቸው የአስተሳሰብና የድርጊት ማእቀፍ የተቻላቸውን ለማድርግ ሞክረው አልፈዋል።
- ሌላውን ትተን ያለፉትን 50 አመታት ብቻ ብንወስድ ሃገርን በመቀየር የህዝብን ህይወት በማሻሻል ስም የተደረጉ ሙከራዎችና ጥረቶች በርካታ ናቸው። «የኔ ቡድን ካንተ ቡድን የተሻለ ለወገንና ለሃገር ተቆርቋሪ ነው። ስለሃገርና ስለወገን ጥቅም ማሰብ የሚያስችል እውቀት ያለው እኔና ቡድኔ ጋር ብቻ ነው። ከኔ በላይ ለሀገሩና ለወገኑ ለመሞትና ለመሰዋት የአላማ ጽናት ያለው የለም። ከኔ ሀገራዊ ራእይ በላይ ላሳር፤ ከእኔ በላይ ህዝባዊ ራእይ ላሳር» በሚል ትንንቅ ባለፈው ሃምሳ አመት በሃገራችን የሰፈነውን ምስቅልቅል፣ የደረሰውን የርስበርስ እልቂት፣ ብዙ ላብ የፈሰሰበት ሃብት ውድመትና ይህንን ተከትሎ የመጣውን ስደትና ውርደት ሁላችንም እናውቀዋለን። አውቀንም ይሁን ሳናውቅ ከተወሰነ የእድሜ ክልል በላይ የሆነው ግለሰቦች፣ በተለይ ፊደል ቆጥረናል የምንለው በሃገራችን ለሰፈኑት ውስብስብ ችግሮች መፍተሄ ከመሆን ይልቅ የችግሩ አባባሾች ሆነን መገኘታችንን መካድ የምንችል አይመስለኝም። አንዱ ግለሰብ ከሌላው፣ አንዱ ቡድን ከሌላው ስለሚሻልበት መከራከር ይቻል ይሆናል። በእዚህም መንገድ ተሄዶ ግን ከጋራ ተከሳሽነት ማምለጥ የሚቻል አይመስለኝም። ማን ከማን ይሻላል የሚለው ጥያቄም ቢሆን ከኛ ትውልድ በስሜት የራቁ የታሪክ ተመራማሪዎች ይፈቱት ይሆናል እንጂ እኛው ባለታሪኮቹ ከሳሽ ተከሳሽ እና እራሳችን ዳኞች በመሆን ብይን የምንሰጥበት ጉዳይ አይሆንም። ለሀገር ለወገን የሚበጀው፣ ወንጀላችንን ወይም ሃጥያታችንን ለማሳነስ ከመሯሯጥና መቋጫ በሌለው ክርክር ግዜያችንን ከምናባክን የጋራ ውድቀታችንን በጋራ ተቀብለን ለራሳችን ለወገናችን የሚበጅ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስርአት እንዴት በጋራ መፍጠር አንችላለን ለሚለው ጥያቄ በጋራ መልስ ለመስጠት መነሳት ነው።

## ሐ) ተስፋ የሚሰጥ ሁኔታ

- ትልቁ ቁም ነገር ተስፋ የሚሰጥ ለውጥ የሚታይበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ሃገራችንና ህዝባችን፣ ሌላው ቢቀር ባፋችን እንኳን ቢሆን ከተመኘንላቸው የሚያኮራ ደረጃ እንዳልደረሱ፣ እንዲያውም በበርካታ ገጽታዎች ወደ ከፋና አሳፋሪ ሁኔታዎች የወረዱ መሆናቸውን ብዙዎቻቸችን አውቀናል።

- ሌላው ቁምነገር በተከታታይ ለህዝቡ እንቆረቆራለን በማለት ህዝብን ሳናማክር በህዝብ ስም ውሳኔ ለመስጠት ስንጣደፍ የነበረበት ዘመን በነውር የተሞላ ዘመን መሆኑን ማየት ጀምረናል።
- ህዝብ በገዛ ሕይወቱ በተለይ በተፈጥሮ ወይም በደመነፍስ ከተቆራኙባቸው የደህንነት፣ የነጻነት፣ የመብትና የጥቅም ጥያቄ ላይ አያውቅም በሚል መመጻደቅ የሃገራችንን ህዝብ በሃገሩና በራሱ ጉዳይ ባይተዋር አድርገን ላየንበት፣ ረጅምና በንቀት የተሞላ ታሪካችን በጋራ ንስሃ እንድንገባ የግንቦቱ ምርጫ ጥያቄ አቅርቦልናል። ብዙዎቻችንም ይህ ጥያቄ ትክክል መሆኑን ተረድተናል።
- የግንቦቱ ምርጫ ያሳየውን የኢትዮጵያን ህዝብ ብልህነት፣ ዴሞክራሲን በአግባቡ በስራ ላይ ለማዋል ያለውን ብቃት በሚገባ ተገንዝበን፣ ቀዳሚ የፖለቲካ አላማችን ህዝብን ተክተን ለመወሰን ሳይሆን ህዝብ መወሰን የሚችልበት እድል ለመፍጠር መስራት መሆኑን መረዳት እንደሆነ ብዙዎች አምነዋል።
- ቅንጅት ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች የበለጠ የህዝብን በሳልነት በመረዳትና በማመን የድርጅቱን የፖለቲካ እጣ ህዝብ እንዲወስነው በህዝብም ላይ አመኔታ አሳድሮ ለምርጫ የቀረበ ድርጅት ነው። ከምርጫው ቀጥሎ ቅንጅት በህዝብ የውሳኔ አቅም በመተማመን በርካታ ውሳኔዎችን የወሰደው ህዝብ በማማከር ነው።
- የኢትዮጵያ ትንሳኤ ክህዝብ የዴሞክራሲ መብቶች መከበር ጋር የተሳሰረ ነው የምንለው ቁጥራችን በርካታ ነው። ህዝብ ነጻነት ቢያገኝ በፖለቲካ ብስለቱ ማስመዝገብ የቻለውን ድል በማህበራዊና በኢኮኖሚ ችግሮቹ ላይ ማስገዘብ የሚችል መሆኑን እውነት የሆነበት ወቅት ላይ ደርሰናል።
- ቀደም ብዬ የጠቃስኳቸውን የመደራጀት አላማዎቻችን ግብ እንዲመቱ ማድረግ የምንችለው ለዴሞክራሲያዊ አመለካከት፣ አደረጃጀት ህግ ደንብና ስርአት ቅድሚያ በመስጠት ብቻ መሆኑን የተረዳው ወገናችን ቁጥሩ እየጨመረ ሄዷል።

***ዴሞክራሲያዊ አመለካከት ዘመን ያመጣው በህዝብ ልብ ውስጥ ቤቱን የሰራ አመለካከት ነው። ይህ እምነት በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ በሚገኘው ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ተዘርቷል። በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝብ የጀመረውን የዴሞክራሲ ጉዞ ሊያስቆመው የሚችል ምንም አይነት ምድራዊ ሃይል አይኖርም።***

*መ) የዴሞክራሲያዊ አደረጃጀት አቅጣጫ በሃገር ቤት*

ህዝብ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ያለውን ፍላጎትና ቅንጅት ስለዴሞክራሲ በማኒፌስቶው ለህዝብ የገባውን ቃል ኪዳን በአንድ ላይ በመደመር በአንድ ወቅት ቅንጅት ወደ አንድ ውሁድ ፓርቲነት ሲቀየር እንዴት አይነት ዴሞክረሲያዊ ድርጅት እንደሚሆን ራእያችንን በአንድ ባለ55 ገጽ ጽሁፍ አስቀምጠን ነበር። ባለፉት 2 አመታት በውጭ የሚገኘው የቅንጅት አንቅስቃሴ ሊመራበት ይገባል ብለን የተሟገትንላቸው ዴሞክራሲያዊ የድርጅት እምነቶች ወደፊት የሃገር ቤቱ የፓርቲው ዴሞክራሲያዊ አደረጃጀት ይከተላቸወል ብለን ካመንባቸው መሰረታዊ ነጥቦች የተቀዱ በመሆናቸው ቁልፍ ናቸው የምላቸውን መጥቀስ እሻለሁ።

ቅንጅት ዴሞክራሲን በሃገራችን ለማስፈን ያለውን ቁርጠኛነት መሰረት በማድረግ ይህንን ቁርጠኛነቱን በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ማረጋገጥ የሚችልባቸው የዴሞክራሲያዊነት መመዘኛ ፈተናዎች እዲያስቀምጥ ጥሪ አቅርበን ነበር። በወያኔ እመቃ ባይቀደም ቅንጅት የተባሉትን ፈተናዎች በሚገባ በማለፍ በሃገራችን እስከ ዛሬ ታይቶ የማይታወቅ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ፓርቲ መዋቅር በሃገር ደረጃ መዘርጋት፣ የፓርቲውንም ተግባራት በላቀ ዴሞክራሲያዊነት መርህ ማከናወን ይችል እንደነበር ጥርጣሬ የለንም።

አንዱና መሰረታዊ የሆነው ለድርጅታችን ያስቀመጥንለት ፈተና፤

***«ራሱን ዴሞክራሲያዊ ማድረግ የማይችል ፓርቲ ሃገርን ዴሞክራሲያዊ ማድረግ አይችልም:: እችላለሁ ቢልም በህዝብ ሊታመን አይገባም::»*** የሚል ነበር::

**ከእዚህም በመነሳት በውክልና ጥያቄ ላይ፣**
የፓርቲው አባላት ወይም ደጋፊዎች በእኩልነት የሚታዩ፣ ሁሉም አንድ ሰው አንድ ድምጽ በሚለው ዴሞክራሲ የመብት እኩልነት ሰንሰለት የተሳሰሩ፣ በድርጅቱ ውስጥ የሚኖራቸው ሃላፊነት አንድ ሰው አንድ ድምጽ በሚሰጥበት ዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሚከናወን እንደሚሆን ነው:: ይህ አንድ ሰው አንድ ድምጽ የሚለው መርህ ውሎ አድሮ ከላይ ከፍተኛ የድርጅቱ መሪዎች አንስቶ አስከመጨረሻው የፓርቲው ድርጅታዊ መዋቅሮች ሁሉ በስራ ላይ የሚውል የውክልና አሰጣጥ አግባብ ይሆናል የሚል እምነት ነበረን:: የፓርቲው የመጨረሻ ቅርጽ አሁን ያለውን በኮታ ከየድርጅቱ የተውጣጣ አመራር ሳይሆን የቅንጅት ውህደት በሃገር አቀፍ ደረጃ ከላይ ወደታች ሲጠናቀቅ በውክልና ከየቀያቸው የሚመጡ የቅንጅት አባላት በሚገኙበት ሃገራዊ ጉባኤ በቀጥተኛ በጉባኤው ተሳታፊዎች በሚደረግ የአመራርና የስራ ሃላፊዎች ምርጫ ይጠናቃቀል የሚል ግምት ነበረን::

<u>የፓርቲና የፓርላማ አባላትን ነጻነት በሚመለከት፣</u>

***«ለፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች በድርጅቱ ውስጥ ነጻነት ለማጎናጸፍ የማይችል ፓርቲ ስልጣን ይዞ ለዜጎች ነጻነት አጎናጽፋለሁ ቢል ሊታመን አይገባውም::»***
የፓርቲው አባላት ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግባቸው ሃሳባቸውን በነጻ የመስጠት የመጠየቅ የመቃወም መብት እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባዋል::
የፓርላማ አባላት በቅድሚያ ተጠሪነታቸው ለፓርላማ መርጦ ላስገባቸው የየወረዳው ህዝብ እንጂ ለፓርቲው አለመሆኑን:: በመረጣቸው ህዝብና በፓርቲው መሃከል ልዩነት ሲፈጠር የመረጣቸውን ህዝብ ፍላጎት የሚያንጸባርቅ ውሳኔ የመወሰን ነጻነትና ግዴታ እንዳለባቸው፤ ፓርቲው በፓርላማ ውስጥ በሚወስዳቸው አቋሞቹ ላይ በነጻነት የመወያየት መጠየቅና የመቃወም መብት እንደሚኖራቸው የሚገልጽ ነበር:: አላማው እንደ ወያኔ የፓርላማ አባላት መለስ ዜናዊ የሚፈልገውን እየተከተሉ እጃቸውን እንደ ሰብአዊ ፍጥረት አካል ሳይሆን እንደ ጭራሮ የሚያንጨባርሩ እንዳይሆኑ ለማድረግ ነበር::

<u>በፓርቲው ስር ስለሚደራጁ የሚድያ ተቋማት ነጻነት በሚመለከት</u>

***«ለፓርቲ ጋዜጣ፣ ድረ-ገጽና፣ ሬድዮና ሌሎችም የፓርቲው የሚድያ ተቋማት በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት የማይሰጥ ፓርቲ፣ ስልጣን ሲይዝ በሃገሪቱ ደረጃ የሚደያ ነጻነት አሰፍናለሁ ቢል ሊታመን አይገባውም::»***

ከእዚህም በመነሳት
የቅንጅት የሚድያ ተቋማት ከፍተኛ የጋዜጠኛነት እውቀትና ተአመኒነት ባላቸው ባለሙያዎች የተሞሉ፣ ተጠሪነታቸው በሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች እንደተለመደው ለማእከላዊ ኮሚቴ ወይም ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሳይሆን እንደ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ ለጠቅላላ ጉባኤ መሆን እንደሚገባው፣ ተግባራቸውም የድርጅቱን ፖሊሲዎች ማስተዋወቅ የህዝብ ግንኙነቱን ስራ መስራት ብቻ ሳይሆን፣ በድርጅቱ ውስጥ የሚነሱትን የፖሊሲ የአመለካከት ልዩነቶች በሰለጠነ መንገድ በማስተናገድ የድርጅቱ

አባላትና ጠቅላላ ህብረተሰቡ እንዲያውቁት ማድረግ፣ በተለያዩ እርከኖች የሚገኙትን የፓርቲው አመራር አካለትን ሆነ ተራ አባል የስነምግባር ጉድለት በሙስና መነከር፣ የፓርቲውን ደንብና ስርአት ራእይና ፕሮግራም የሚያፋልሱትን በሙሉ በመረጃና በጥናት በመደገፍ በሚያቀርበው ዘገባ በየትኛውም ሃገር የሚገኝ ነጻ ፕሬስ የሚጫወተውን የዴሞክራሲ ጠበቃነት ሚና እንዲጫወት ማስቻል ነው።

<u>በእድሜ በጾታና በሌሎችም ፍላጎቶች ዙሪያ ስሚቋቋሙ ድርጅታዊ አካላት።</u>

***«በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ስር ለሚቋቋሙ የወጣቶች ሆኑ የሴቶች ድርጅቶች ወይንም ቅንጅትን ለመደገፍ ለሚቋቋሙ ሌሎች አካላት በነጻነት እንዲደራጁና እንዲንቀሳቀሱ መብት የማይሰጥ ድርጅት ስልጣን ይዞ ለሲቪክና ለሙያ መህበራት በነጻ መደራጀት መብት እሰጣለሁ ቢል ሊታመን አይገባውም።»***

ከእዚህም በመነሳት

በውጭ ሃገር የሚደራጁ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች በራሳቸው ፍላጎት የተሰባሰቡ ግለሰቦች ስብስብ መሆናቸውን በመረዳት በከፍተኛ ነጻነትና ዴሞክራሲያዊነት ተደራጅተው መንቀሳቀስ እንዳለባቸው የሚያምን ራእይ ቅንጅት አለው።

አንዳንዶቻችን ከእዚህ በላይ የጠቀስናቸውን ሃሳቦች ከቅንጅት ማኒፌስቶ በቀጥታ የሚቀዱ ናቸው የሚል እምነት አለን። ሁኔታው በሚፈቅደው መጠን እነዚህ የቅንጅተ ዴመክራሲያዊ እሴቶች በቅንጅት የውጭ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲዘሩ ማድረግ ችለናል። እንቅፋቱ በዝቶ የታበውን ያህል ግን መራመድ እዳልቻልን በአለም ዙሪያ የተበተኑ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶችና አባሎቻቸው በሚገባ ያውቁታል። ይሁንና የመሪዎቻችን መፈታት ይህንን ሂደት የመያጠናክረው እንጂ የሚቀለብሰው አንደማይሆን ልባችንን መልተን ማገር እንችለለን።

<u>*ሠ) ከሃገር ውጭ ያለውን የቅንጀት እንቅስቃሴ በሚመለከት*</u>

- *የውጭ ሃገሩ እንቅስቀሴ የሃገር ቤቱ ክፋይ ነው ። አለማው ተመሳሳይ በሆነ መንገድ እንደ ሀገር ቤቱ ፓርቲ ኢትዮጵያውያን በከፍተኛ ነጻነትና ዴሞክራሲያዊነት በመቶሽዎች የሚሰባሰቡበት እንቅስቀሴ መፍጠር ነው።*
- *የእዚህ እንቅስቃሴ ግቡ ወያኔን ከስልጣን ለማውረድ የሚደረገውን ትግል መደገፍ ብቻ አይደለም። የኢትዮጵያን ህዝብ የዘመናት ህልም የሚያሳካ የወገንና የሃገር ተቆርቋሪነት ያለው ጠንካራ የኢትዮጵያውያን የትብብር አንቅስቃሴ መመስረት ነው።*

- *ይህ እንቅስቀሴ አላማው በፖለቲካ ዙሪያ የሚመዘገቡ ድሎችን ማስቀጠር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ በማህበራዊና በኢኮኖሚ ችግሮቹ ዙሪያ በአጭር ግዜ ውስጥ ታላላቅ ድሎችን ማስመዝገብ እንዲችል ከፍተኛ እገዛ ማድረግ ነው። ይህንን ለማድረግ የውጭው አንቅስቃሴ ባለፉት ሰላሰ አመታት ተቀፍድዶ ከኖረበት የተሳሳቱ የአደረጃጀትና የአመለካከት ችግሮች ነጻ መሆን አለበት።*

***ሁላችንም ልንግባባቸው የሚገቡ መሰራተዊ ነጥቦች መሃል በጥቂቱ ልጥቀስ***

- *ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በተግባር ሌላ ድርጊት ፈጽሞ እስካልተገኘ ዜግነቱ ባለበሰው ስብእናው ለሃገሩ የሚቆረቆር ሃገሩን የሚወድ መሆኑን መቀበል፣ አንዱ ከአንዱ የተለየና የበለጠ ኢትዮጵያዊነት የሌለው መሆኑን በመቀበል ለኢትዮጵያ መቆርቆር የሁሉም ዜጎቿ መብትና ነጻነት እንጂ ለጥቂት ምርጦች በመለኮት የተበረከተ አለመሆኑን መረዳት፣*

- ኢትዮጵያውያን በዜግነታቸው የማይበላለጥ ስብእና ያላቸው ግለሰቦች መሆናቸውን በመረዳት፣ ሁሉም በጋራ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ውስጥ እየአንዳንዱ ግለሰብ ከአንድ ግለሰብ ያልበጠ ያላነሰ ሁሉም በእኩልነት የሚታዩ መሆናቸውን መረዳት፣
- ግለሰቦች በእውቀታቸው በጉልበታቸው በሃብታቸው በጊዚያቸው የተላያዩ እንደሆኑ ተገንዝቦ፣ ሁሉም በአቅሙ ለሚያበረክተው አስተዋጽኦ እኩል ክብር፣ እኩል ክብደት እንዳለው በመረዳት ሁሉንም የመንከባከብ አስፈላጊነትን መረዳት:: ትልቁ ቁም ነገር የግለሰቦች አስተዋጽኦ ይብለጥም ይነስም ሁሉም ኢትዮጵያዊ እራሱን የእንቅስቃሴው አካል አድርጎ እንዲያይ ማድረግ ይሆንበታል:: የብዙሃኑ ትንንሽ አስተዋጽኦዎች ተደምረው ትግሉን በከፍተኛ ደረጃ የሚያግዝ የእውቀት የገነዘብና የጉልበት ክምችት መፍጠር እንደሚችል ማረዳት ይኖርብናል
- በአስተዋጽኦ ደረጃ እየተለካ የሚመጣ የመብት መበላለጥ እንደማይኖር፤ በእዚህ ትግል ውስጥ ስንገባ ባዋጣነው የግዜ፣ የገንዘብ፣ የመስዋእትንት አስተዋጽኦ እየተሰፈረ የሚከፈለን ወሮታ እንደማይኖር፣ የምንታገለው ለስምና ለዝና ለሹመትና ለሽልማት እንዳልሆነ መረዳት ይኖርብናል::
- ልክ እንደሃገር ቤቱ በውጭ ሃገር በሚገኘው የቅንጅት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚወስድ ሃላፊነት፣ የእንቅስቃሴው አባላት በፍላጎታቸው ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን ተጠቅመው የሚሰጡትና መልሰው የሚወስዱት መሆኑን መረዳት:: ስልጣን በውክልና የሚሰጥና የሚወሰድ ርስተ-ጉልት ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ነገር አለመሆኑን መረዳት አለብን
- ጥንታዊ አደረጃጀትን ከዘመናዊ አደረጃጀት የሚለየው ጉዳይ ግለሰቦች የመጡበት ጎጥ፣ ዝምድናቸው ጉርብትናቸውና ጓደኛነታቸው ሳይሆን ለሃገርና ለወገን ይጠቅማል በሚሉ ሃሰቦች ዙሪያ መሰባሰብና አንድነት መፍጠር መቻላቸው መሆኑን በመረዳት፣ ቅንጅት የጀመረውን የዴሞክራሲ እንቅስቀሴ በጠባብ ምክንያቶች የተሰባሰቡ ግለሰቦች ብቻ የሞሉበት እነዚህ ሃይሎች ብዙሃኑን አግለው ብቻቸውን እንዳሻቸው የሚዘውሩት እንዳይሆን ጠንቅቆ መጠበቅ ይገባናል::
- እያንዳንዱን ግለሰብ የሚገዛ ዴሞክራሲያዊ ህግ፣ ደንብና ስርአት ያለው እንቅስቃሴ በመፍጠር ማናቸውም የእንቅስቀሴው አካል፣ ከፍተኛ ስልጣን ካለው እስከ ዝቅተኛው፣ ከፍተኛ የገንዘብ የእውቅት የጊዜ የጣርና የመከራ መስዋእትነት የከፈለም ሆነ በትንሹ አስተዋጽኦ ያደረግም ቢሆን በእዚህ ህግና ደንብ የሚገዛበትን ሁኔታ አስገዳጅ አድርጎ ለመንቀሳቀስ መጣር፣
- አላማችን በእንቅስቃሴያችን ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ለማስደሰት ሳይሆን ከቡድኖችና ከግለሰቦች ፍላጎት በላይ ታላቅ ከሆነ የሃገርና የወገን ጉዳይ ጋር የተሳሰረ መሆኑን መረዳት::
- ትልቁን የነጻነትና የዴሞክራሲ ክንፍ አጥልቀው እንደ ንስር አሞራ በወያኔ አናት ላይ መብረር እየቻሉ በኋላ ቀር ባህሎች ተተብትበው እንቅስቃሴውን እንደብል እየበሉ ለመኖር የሚፈልጉ ግለሰቦችን ትርጉምና ቦታ የሚያሳጣ አድርገን እንቅስቃሴያችንን በብዙሃን ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ላይ መገንባት ይጠበቅብናል:: ጥቂት ግለሰቦች ሲያኮርፉ፣ ሲቆጡና ሲከፉ የሚፈርስና የሚጠፋ ድርጅት መሆን የሌለበት መሆኑን ማረጋገጥ አለብን:: ስለሃገራችን የምናስበው የምንቆረቆረው ለመሪዎቻችንና ለጓደኞቻችን ብለን አይደለም:: ቀደም በዬ እንደገለጽኩት ለራሳችን፣ ላለፉት ቀደምቶቻችን ለልጆቻችን እና ለመጪው ትውልድ መሆኑን ሁሌም ማስታወስ ያስፈልጋል::
- ዴሞክራሲያችን ጠንካራ ስላልሆነ ትእግስትን፣ ግዜ አጥፍቶ መከራከርን መማከርንና መቻቻልን የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳት መሰረታዊ ባለሆኑ ጉዳዮች ላይ አላስፈላጊ የሆነ የጎራ ልዩነት እየፈጠሩ መናቆርን ከማራባት መቆጠብ ይገባናል:: የኢትዮጵያ ህዝብ የመብትና የነጻነት ቀበኞች ጥንካሬ ያገኙት በራሳቸው ሳይሆን እኛ በአንድነት አለመቆማችን እንደሆነ ነው:: መሪዎቻችንና ብዙዎቻችን አንድነት አንድነት የምንለው መከፋፈላችን የመጣውን ጉዳት

ጠንቅቀን በማወቃችን ነው፡፡ በአንድነት ጉዳይ ተደጋጋሚ ችግሮች የገጠሙን ሁላችንንም በጋራ የሚገዙ በጋራ የተስማምናባቸው መሰረታዊ ህጎችና ደንቦች መቅረጽና ለእነዚህ ደንቦች ተገዥ በመሆን የመስራት ባህል ማዳበር ስላልቻልን ነው፡፡ አንድነታችን እንዲጠናከር ከስሜት አልፈን በተግባር ምን ማድረግ አለብን በለን መጠየቅ ይኖርብናል፡፡ በሌላ በኩል ትግሉን የሚጎዱ፣ ቅንጅ በማኒፌስቶው ለህዝብ የገባውን ቃልኪዳን የሚያፋልሱ የመርህ ጥሰቶች ሲነሱ ግልጽና ቁርጠኛ ነት ያለው አቋም በአደባባይ ለመውሰድ ዝግጁነት እንዲኖረን ማድረግ አለብን፣

- ከእዚህ በኂላ በሃገራችን ውስጥ የሚደረገውን የነጻነትና የዴሞክራሲ ትግል ለመደገፍ በውጭ ሃገር የሚደረገው እንቅስቃሴ ራሱ በቀደደው የዴሞክራሲ ቦይ ብቻ የሚፈስ ይሆናል፡፡ እየተሰበሰባችሁ አጨብጭቡልኝ፣ እየተሰበሰባችሁ ገንዘብ እያወጣችሁ ስጡን፣ እየተሰበሳባችሁ ጩሁልኝ የሚልን የማንኛውም አዛዥ ትእዛዝ በጭፍኑ አይቀበልም፡፡ ባለፉት ሁለት አመታት በአለም ላይ የተደራጁት የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች የተደራጁት የኢትየጵያ ህዝብ ደሙን በገበረለት በመቶ ሽዎች ለታሰረበትና ለተሰደደበትም፣ መሪዎቻችንም ቀልኪዳናቸውን ጠብቀው በእስር መከራቸውን ላዩበት በቅንጅት ማኒፌስቶ ውስጥ ባሰፈሯቸው መርሆዎችና እሴቶች ላይ ነው፡፡ በቅንጅት ማኒፌስቶ ውስጥ የሰፈረውን የዜጎችን ግዴታ፣ ሃላፊነትና መብት በሚገባ በተረዱ የቅንጅትን የተጠያቂነት፣ የግልጽነትና የተጠሪነት መርሆች ባነገቡ ግለሰቦች ነው፡፡ በእዚህ አይነቱ የዴሞክራሲያዊ እምነት መሰረት ለማንም ኢትዮጵዊ ከእዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ክፍትነት ከተደራጁና ለመደራጀት ፍላጎት ካላቸው የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶችጋር መሄድ ያልቻሉት እንደቀድሞ ዘመን በሴራ በተንኮል በድርጅታዊ አሰራር ሳይሆን በአደባባይ በፈጸሙት ነውር፣ በድርጊታቸው በሰፊው ህብረተሰብ ተተፍተው በአለምዙሪያ ተንሳፈው ተቀምጠዋል፡፡ በውጭ ሃገር የሚገኘው እንቅስቀሴ ከወያኔ ከሚወረወር ጥቃት በከፋ መልኩ የተጎዳው፣ በየሃገሩ ለራሳቸው የተጋነነ ቦታ ሰጥተው፣ ብዙሃኑን በሃገሩ ጉዳይ እንዳይሳተፍ፣ ሁሉን አዋቂ ሁሉን ፈጻሚ ነን በማለት ከተራ አምባገነን ብዙም ልዩነት በሌለው መንፈስ በተንቀሳቀሰሱ ሰዎች ነው፡፡ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሳይሆን በድንጋጌ «እኔ ጌታ ካልሆንኩ፣ እኔን የሚያክል ሰው እንደተራ አልባሌ ፍጥረት የድጋፉ ድርጅት የአባልነት ፎርም እንዴት እሞላለሁ፣ እኔን የመሰለ አዋቂ እንዴት ከማንም ኩታራ ጋር ለምርጫ እቀርባለሁ፣ እኔ አዛዥና ናዛዥ ካልሆንኩ የቅንጅት እንቅስቀሴ አፈር ይብላ፣ የታሰሩት በእስር ይበስብሱ፣ የሞቱትም ደማቸው ደመ-ከልብ ሆኖ ይቅር የሚሉ ጥቂት ግለሰቦችን በየሃገሩ አይተናል፡፡ እንዲህ አይነቶቹ ግለሰቦች አሁንም ማወቅ የሚገባቸው ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ለእንዲህ አይነቱ አመለካከታቸው ቦታ የሌለው መሆኑ ነው፡፡ የምንገኘው በዘመነ መሳፍንት ሳይሆን በዘመነ ዴሞክራሲ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ አመለካከት ካላቸው ግለሰቦች የቅንጅት የውጭ እንቅስቀሰሴ ራሱን ለመከላከል ነቅቶ መጠበቅ ይገባዋል፡፡ እነዚህ ግለሰቦችም የዘመኑን መቀየር ተረድተው ለዴሞክራሲያዊ አደረጃጀት አሰራር መንፈሳቸውን አስገዝተው በጋራ በእኩልነት መቆም ብንችል ተጠቃሚው ሁላችንም ሃገራችን እና ወገናችን በመሆኑ ኂላ ቀር አመለካከታቸውን አራግፈው ከጎናችን ቢቆሙ ዛሬም ነገም እጃችንን ዘርግተን ወገናዊ አቀባበል እንደምናደርግላቸው ሊያውቁት ይገባል፡፡
- ባለፉት ሰላሳ አመታት በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ በመግባት በመሰላቸው መንገድ ብዙ ትግል ያደረጉ ግለሰቦች እንዳሉ እናውቃለን፡፡ ዛሬ በቅንጅት ውስጥም ያሉ ግለሰቦች በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ብዙ መስዋእትነት የከፈሉ እንዳሉ እናውቃለን፡፡ ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች የከዚህ ቀደሙ ትግላቸው ዛሬ እንደምናየው ከሃገር ውጭ ያለውን ህዝብ ዳር እስከዳር አንቀሳቅሶት አያውቅም፡፡ ለእዚህ ምክንያቱ ቅንጅት ይዞት የመጣው አጠቃላይ ራእይ መሆኑን፣ ቅንጀት በሃገር ቤት ባለው ህዝብ ያገኘው አመኔታ መሆኑን፣ መሪዎቹ መከራ በገፍ በሚመረትበት ሃገር ውስጥ በመገኘት ለመስዋእትነት ቆርጠው የተነሱ የጀግንነት አርአያዎች በመሆናቸው ነው፡፡ ከሃገር ውጭ ከፖለቲካ ርቆ ይኖር የነበረው

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ሆ ብሎ ቅንጅትን ለመደገፍ መነሳቱ የቆዩትን ታጋዮች ሊያስደስት ሊያስፈነጥዝ ይገባዋል:: በብዙ ቦታዎች የታየውም ይህ ነው:: ይሁንና ይህ በስፋት የመጣ ኢትዮጵያዊ የቅንጅትን ራእይና መርህ አንግቦ መንቀሳቀሱ ሽብር የፈጠረባቸው ጥቂት ግለሰቦች በየቦታው አይተናል:: እነዚህ ወገኖቻችን ብዙዎቻችን ምንም ማድርግ ባልቻልንበት ወቅት ለከፈሉት መስዋእትነት የሚስማንን ባለውለታነት አክብሮት ከልባችን ልንገልጽላቸው ይገባናል:: ነገር ግን እንደ ሃሽሽ ነጋዴ «በኔ ቀጠና፣ በኔ turf ለምን ትደርሳላቸሁ? ምን አገባቸሁ? ከመጣቸሁም የኔን ቀጭን ትእዛዝ እየተቀበላችሁ መሰማራት ይገባችኋል የሚል አመለካከታቸው ፍጹም ስህተት መሆኑንና በዘመነ ዴሞክራሲ ቦታ የሌለው መሆኑን ልንነግራቸው ይገባል:: ይህ ዝንባሊያቸውና ድርጊታቸው ቆመንለታል ከሚሉት የሃገርና የወገን ጉዳይ ጋር የሚቃረን መሆኑን ልናስረዳቸው ይገባል::

- ከሁሉም በላይ በሃገርና በወገን ጉዳይ ለመቆርቆር፣ ለትግሉ አስተዋጽኦ ለማድርግ የማንንም ቡራኬ ወይም ፈቃድ የማንጠይቅ፣ የዜግነት ግዴታችንና መብታችን መሆኑን፣ «ከእኛ ፈቃድ ውጭ እስኪ ነቅነቅ በማለት ሊያስፈራሩን ለሚዳዳቸው» ጉደኞች ማስገንዘብ ይኖርብናል::
- የውጭው እንቅስቃሴ ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተሰነዘረበትን ጥቃት ተቋቁሞ እዚህ ደርሷል:: መሪዎቻችን በመታሰራቸው ለምስክርነት የሚጠሩበት ሁኔታ እንዳሌለ በማወቅ ውዥንብር ሆን ብሎ በመንዛት፣ በስማቸው በመማልና በመገዘት በድርጅታችን ላይ ጉዳት ያስከተሉ ጥቃቶች ተሰንዝረዋል:: አሁን ግን ይህን ማድረግ አይቻልም:: ከመሪዎቻችን ጋር የተፈታው እውነት ብቻ ሳይሆን፣ በቅንጅት ውስጥ ስለእውነት የመናገር ነጻነታችን ነው:: ከቅንጀት እምነት ጋር ያልተገናኙ፣ዘረኛና ከፋፋይ እምነቶችና አስተያየቶች ሲዘነዘሩ፣ ጸረ-ዴሞክራሲያዊ የሆኑ ድርጊቶች ሲፈጸሙ፣ ግለሰቦች በድርጅቱ ገንዘብና ሃብት፣ መልካም ስምና ዝና ያለተጠያቂነት ከፍተኛ ወንጀል ሲፈጽሙ በዝምታ ያለፍንበት ዘመን አብቅቷል:: ከማንኛውም ነገር በእስር የሚማቅቁ መሪዎቻችን አንድነታችንን የሚፈልጉ በመሆናቸው ከፍተኛ የዴሞክራሲ መርህ የሚጥሱ ግለሰቦችን እሹሩሩ ብለን ለማለፍ ተገደን ነበር:: ይህንን የሚፈጽሙትን ግለሰቦችና ቡድኖች ፊት ለፊት በመናገር፤ በመርህም ላይ የተመሰረተም እንኳን ቢሆን፤ እነዚህን ግለሰቦችና ቡድኖች በመተቸት የሚመጣው መቃቃር መሪዎቻችን ያስከፋል በሚል እምነት ሰምተን እንዳልሰማን፣ አይተን እንዳላየን ብዙ አሳልፈናል:: ይህ ዘመን ግን ከመሪዎቻችን መፈታት ጋር አክትሟል:: መሪዎቻችንን በቅንጅት ማኒፌስቶ አማካይነት ለህዝብ የገቡትን ዴሞክራሲያዊ ድርጅት የማቆምና ዴሞክራሲያዊ አሰራር የማስከበር ሃላፊነት አለባቸውም:: በእስር በነበሩበት ወቅት በውጭው እንቅስቃሴ ውስጥ የታዩትን ቅንጅታዊ ያለሆኑ አሰራሮች ተግባሮች ባህርዮች ባስቸኳይ እንዲታረሙ አድርገው ለዴሞክራሲ ለሚደረገው ትግል ግንባር ቀደም መሆናቸውን እንደሚያረጋግጡም እርግጠኞች ነን:: በብዙ ነገሮች ላይ መደራደር ይቻላል:: በውጭ የሚገኘው የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች እንቅስቀሴ በመሰረታዊ የዴሞክራሲ መርሆዎች ላይ ግን መደራደር አይገባውም:: በእዚህ ላይ የሚታይ ለቀቅተኛነት በውጭ የተጀመረውን ዴሞክራሲያዊ ትግል አጫጭቶ ይህንን አደገኛ መርዝ ወደ ሃገር ቤት ኤክስፖርት ማድረጉ አይቀርም:: በእዚህ መንገድ ከተጓዝን የትግላችን ወጤት አንዱን ዘረኛ በሌላ ዘረኛ፣ አንዱን አምባገነን በሌላ አምባገነን፣ አንዱን ቀማኛ በሌላ ቀመኛ መተካት ብቻ ይሆናል:: «የሃገራችን ጉዳይ የራሳችን ጉዳይ፣ የወገናችንም ጉዳይ የራሳችን ጉዳይ ነው» በማለት ለራሳችን ለቤተሰቦቻችን ለዘመዶቻቻን ለወገናችን ስንል ይህንን ትግል የተቀላቀልን በሙሉ ያለምንም ይሉኝታ፣ ያለምንም አድርባይነት መሰረታዊ የሆኑ ጸረ ዴሞክራሲያዊ ዝንባሌዎች በቅንጅት ውስጥ አንገታቸውን ቀና እንዳያድርጉ ማድረግ ይኖርብናል:: አሁንም በውጭው የኢትዮጵያውያን እንቅስቃሴ ውስጥ፣ በቅንጅት አካባቢ ሆነ ከቅንጅት ውጭ በሚንቀሳቀሱ የፖቲካ

ሃይሎች ውስጥ፤ ተመክሮ፣ ስልጣኔ ማየት፣ የሃገርና የወገንን ጣር መብዛት፣ ከየትምህርት ተቋማቱ የአዋቂነት መረጃ መቀበል ያልገራውን ኋላ ቀር የጉልተኛ ና የጨለማ ዘምን ፖለቲካ ተሸክመው እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል በሚል ፈሊጥ በአፍራሽ ተልእኳቸው የሚቀጥሉትን በሙሉ አቁሙ ልንላቸው ይገባል:: የሚቀልዱትና የሚያሾፉት በግል ገንዘባቸው ከየሱቁ በገዙት አሻንጉሊት ሃገር ላይ ሳይሆን በሁላችንምና ሚሊዮኖች መስዋእትነት እየከፈሉ ባቆዩዋት የሁላችንም እናት በሆነችው በኢትዮጵያ ላይ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል:: ዛሬ በቅንጅት ዙሪያ የተሰበሰበው ኢትዮጵያዊ እንደ አለፉት ዘመናት በወሬና ባሉባልታ የማይፈታ ማንኛውንም ችግርና ፈተና በማሸነፍ ከነጻነትና ከዴሞክራሲ አምባ ከመድረስ ውጭ ሌላ አማራጭ የሌለው መሆኑን በማያወላዳ ቋንቋ ለሚጠራጠሩት ሁሉ መግለጽ ይገባዋል::

- ዛሬ በውጭ ሃገር የሚገኘውን የድጋፍ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ለመምራት የተሾምኩ ነኝ፣ የፓርቲ አለቃ ነኝ፤ የኅበዝ አለቃ ነኝ የሚባልበት ዘመን አብቀቷል::
- ጥቂት ግለሰቦች በፓርቲ አለቃነት፣ በሹመኛነት ተቀምጠው፣ ኢትዮጵያዊውን ሰልፍ እንዲወጣ ሲፈልጉ፣ ሰልፍ ውጣ ብለው አስወጥተው የሚበትኑበት፤ ገንዘብ ሲፈልጉ፣ የገንዘብ ስብሳበ አካሂደው የሚበትኑበት፤ እውቀቱን ሲፈልጉ ተጠቅመውበት እንደ ሸንኮራ መጠው የሚተፉበት፤ በሰበሰቡት ገንዘብ ያለተጠያቂነትና ያለተጠሪነት እንዳሻቸው የሚያደርጉበት ሁኔታ አብቅቷል::
- ኢትዮጵያዊ በበረዶ፣ በዝናብና በጸሃይ ሰልፍ የሚወጣ ከሆነ፣ ከልጆቹ ከቤተሰቦቹ ጉርስ እየቀነሰ ላቡን አንጠፍጥፎ ያገኘውን ገንዘቡን የሚያዋጣ፤ እውቀቱን ግዜውን የሚያበረክት እስከሆነ፣ እንዲህ አይነቱን የላቡ የጉልበቱ የገንዘቡ የእውቀቱ ውጤት የሆነውን እንቅስቃሴ የማይቆጣጠርበት ምንም አይነት ምክንያት አይኖርም:: ይህንን ማድረግ ተጀምሯል:: የድጋፍ ድርጅቶች ዴሞክራሲያዊ አደረጃጀት ለአባላቱ እንዲህ አይነቱን የባለቤትነት ስሜት ያላበሰ አባላቱን በሃገራቸው ጉዳይ ከዳር ተመልካችነት ወደ ቀጥተኛ በላቤትነት ያሸጋገረ ስልት ሆኗል:: የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር የተመኘውን ያህል ባይሰራም በአለም ላይ ባሉ የድጋፍ ድርጅቶች ትብብርና ድጋፍ፣ ሌላው ቢቀር መሪዎቻችን ሲፈቱ ሊረከቧቸው የሚችሏቸው በርካታ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተደራጁ ለቅንጅት ቀናኢ የሆኑ የድጋፍ ድርጅቶች በአለም ዙሪያ እንዲደራጁ ማድርግ ችሏል:: እነዚህ የድጋፍ ድርጅቶች ቃል ኪዳናቸው ከቅንጅት ጋር ነው:: ታማኝ ነታቸው ለቅንጀት ብቻ ነው:: ባለፈውም ሁለት አመት ያደረጉት ትግል ቅንጅትን እንደድርጅት የሚያጠብቅ፣ መሪዎቻችን በአንድነት እንደታሰሩ በአንድነት ተፈተው በጋራ የጀመሩትን ትግል ከግቡ ለማድረስ በጋራ አመራር እንዲሰጡን ለማስቻል ነው:: የወደፊቱም ምኞታቸውም ይህ ብቻ ነው::
- የተቻለንን ሰርተን የተሰጠን ሃላፊነት ከእስር ለተፈቱት መሪዎቻችን አስረክበናል:: ብጹእ እንዳልሆንን እኛም እናንተም ታውቃላችሁ:: ለተሳሳትናቸው ስህተቶች ጸጸትን በልባችን ይዘናል:: ባለፈው አስቸጋሪና ፈታኝ ወቅት ያስቀየምናቸው በዙ እነደሚሆኑ ስለምናውቅ ይቅርታን ከልባችን እንጠይቃለን::
- አዎን ዛሬ የስንብት ቀን ነው:: በቅንጅት አለም አቀፍ አመራሩ ውስጥ የነበርን ሰዎች ካጠገባቸሁ እራቅን አልራቅንም በድጋፍ ድርጅቶች አካባቢ የተጀመረውን የዴሞክረሲያዊነት ሂደት የሚያስቆመው ምድራዊ ሃይል አይኖርም:: የአለም አቀፉ የፖለቲካ አመራር ትለቁ ሽልማቱና ጌጡ ይህ ነው:: ይህ የዛሬው በአል ይህንን ዴሞክራሲያዊ ድል እንደሚያወድስ አድርጌ እወስደዋለሁ::

## ረ) ኩራት

ኮራሁኝ

- ኢትዮጵያውያን የተለየን ፍጥረቶች ነን ስንል ብዙዎቻችን ቶዳችንን ዝም ብለን ስናዋድደው ይመስለን ነበር:: ግን አይደለም:: በአፍሪካ ምድር በሃገራችን በቅርቡ ከደረሰው እልቂትና ግፍ በላይ በርካታ ጉድ ታይቷል:: በሩዋንዳ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚሆን ህዝብ አልቋል:: በኮንጎ፣ በሱዳን፣ በናይጄሪያ፣ በዩጋንዳ በሌሎችም የአፍሪቃ ሃገሮች በአስር ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በየግዜው አልቀዋል:: ታስረዋል:: ተሰደዋል:: የየትኛዎቹም ሃገር ዜጎች ግን በሰላሳና በአርባ በሚቆጠሩ የአለም ከተማዎች ለሁለት አመት ያልተቋረጠ የተቃውሞና ሰልፍና እንቅስቃሴ ያደረገ አይገኝም:: ማዳመጥ፣ መመዘን፣ በራሳችን ውሳኔ መስጠት የምንችል፣ ወደ ፊትም ተአምር መስራት የማይሳነን ለመሆኑ ያለፉት ሁለት አመታት ፍንጭ ሰጥተውን አልፈዋል:: ይህንን ለማድረግ እኛም ሆነ የሃገራችን ህዝብ የሚጠብቀው አንድ እድል ብቻ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን::
- በምርጫ ግዜ እድለኛ ሆኜ በሃገር ቤት ያየሁትን የኢትዮጵያውያን የታላቅ ህዝብነት መንፈስ በውጭም መደገሙ፣ የኢትዮጵያ ትንሳኤ የግዜ ጉዳይ እንጂ አይቀሬ መሆኑን የማይናወጥ እምነት ሰጥቶኛል::
- ኩራቴ በእዚህ አዳራሽ ውስጥ ባላችሁት ብቻ አይደለም:: በሰለፍ በሻማ መብራት ከጎናችን በቆሙት ብቻ ሳይሆን፣ ገንዘባቸውን እውቀታቸውን ባዋጡት ብቻ ሳይሆን፣ እንዲያው በኢትዮጵያዊነታቸው በመንፈስና በልባቸው ከኛ ጋር የነበሩት በተለያየ አጋጣሚ ስናገኛቸው አብረውን መሰለፍ ባለመቻላቸው ሲጨነቁ ያየናቸውን በመቶ ሽዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን ያካትታል:: የእናንተና የእነዚህ ሁሉ ኢትዮጵያውያን ወገን በመሆኔ ኮራሁኝ:: እንናንተም ያለመታከት በጽናት ከባድ ፈተናዎችን አልፋችሁ መሪዎቻችንን አስፈትታችሁ ለነጻነት፣ ለፍትህና ለዴሞክራሲ ለሚደረገው ሌላ ዙር ትንንቅ በተጠንቀቅ በመቆማችሁ ልትኮሩ ይገባል::

## ሸ) ምስጋና

- ወያኔ በቅንጅት ላይ በወሰደው በግፍ የተሞላ እመቃ የተነሳ ቅንጅትን በሃገር ቤት ያለአመራር ያስቀረው ሁኔታ ፈጥሮ ነበር:: ይህንን ሁኔታ ገና በጥቅምት 1998 ኢ.ም በመረዳት ቅንጅት የጀመረውን ትግል ለመቀጠል የውጭው የድጋፍ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሃላፊነት እንደሚወድቅበት በእንግሊዝ ሃገር ለሚገኘው የድጋፍ ድርጅትና በተለያዩ ሃገሮች ለማውቃቸው የድጋፍ ድርጅቶች አባላት ለማስጠንቀቅ ሞክሬ ነበር:: የውጭውም እንቅስቃሴ በሚገባ ያልተደራጀ የሚደራጅበትንም መሰረታዊ መርሆዎች በሚገባ የተገነዘበ ያልነበረበት፣ ቅንጅትን ለመደገፍ በሽዎች የሚወጣውን ህዝብ በድርጅታዊ መዋቅር ስር እንዴት መሰብሰብ እንደሚቻል ራእዩ የሌላቸው ግለሰቦች በእንቅስቃሴው አናት ላይ ተፈናጠው፣ ውሎ አድሮም የውጭው እንቅስቃሴ እጣው መክሰም ሆኖ በሚታይበት ወቅት ነበር የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር እስርቤት በሚገኙት የድርጅቱ መሪዎች ፈቃድ የተቋቋመው:: የአለም አቀፍ አመራሩ አቋቋም ዴሞክራሲያዊ እንዳልሆነ በወቅቱ ብዙዎች ያነሳችሁት ጉዳይ ነበር:: በበኩሌ ቅንጀት የሚገኝበት ሁኔታ በማጣቀስ እንዲህ አይነቱን የፖለቲካ አመራር በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመሰየም የማይችል መሆኑን ከመግለጽ ውጭ አመጣጣችን ዴሞክራሲያዊ ነው በማለት ተከራክሬ አላውቅም:: ቅንጅት ከገባበት አጣብቂኝ በመነሳት ይህ አካል አስፈላጊ መሆኑን፣ በሂደትም የሚቀየር ወይም የሚከስም መሆኑን ከማቅረብ በስተቀር አለም አቀፍ አመራሩ ለህልውናው ዴሞክራሲን በማጣቀስ የሚያቀርበው መከላከያ አልነበረውም:: በተለይ ከመጀመሪያው እንደታሰበው ለጥቂት ግለሰቦች ሃላፊነት ተሰጥቶ፣ በውጭ ከሚገኘው የቅንጅት ደጋፊ ጋር በመመካከር ታስቦ የነበረው አመራሩን የማቆም

> ሃሳብ «እኔ ካልገባሁበት በሚሉ ግለሰቦች ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ ተገፍቶ፣ ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ ላኪዎቹና ሌሎችም ግለሰቦች ተጨምረው የተቋቋመው የአለምአቀፍ አመራር ለናንተም ብቻ ሳይሆን፤ ከዴሞክራሲያዊ መርህ አኳያ ሲቃኝ፤ ለሁላችንም አሳፋሪ እንደነበር መካድ አይቻልም:: ስለቅንጅት የፖለቲካ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊነት ብዙ ስጽፍና ሳወራ ለቆየሁት ግለሰብ ይህ ሂደት ያልጎመዘዘኝና እንዲያው በደስታ የተቀበልኩት ጉዳይ አልነበረም:: ብዙዎቻችሁ ወቅቱን ግምት ውስጥ በማስገባት ከዴሞክሲያዊነት መስፈርት ውጭ የቀረቡትን ምክንያቶች ተቀብላችሁ፣ ከሁሉም በላይ ስለአለም አቀፍ አመራሩ በርካታ ውዥንብር በሚነዛበት ሁኔታ፣ መሪዎቻችን ፈቀዱም አልፈቀዱም ትግሉን የፖለቲካ አመራር በመስጠት የሚያስተባብር አካል ያስፈልጋል በሚል ቀና መነሻ ልንደግፈው ይገባል ብላችሁ ለደጋፋችሁን ምስጋና አቀርባለሁ:: ለናንተ ከደቡብ ኮርያ እስከ አውስትራሊያ፣ ከአሜሪካ እስከ መካከለኛ ው ምስራቅ፣ ከአውሮፓ አስከ አፍሪቃ፣ በሚገኙ ከተሞች ለምትኖሩ በሽዎች ለምትቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በአለም አቀፍ አመራሩ ስም ምስጋና አቀርባለሁ:: ማለቂያ በሌለው አለመተማመንና መጠራጠር ላይ የቆየውን ባህላችን በጣጥሳችሁ «የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ከመሪዎቹ ፍላጎትና እውቅና ውጭ የተቋቋመ አካል ነው» የሚል ሃሰት፣ እውነቱን ማወቅ በሚገባቸው ግለሰቦች ጭምር ሲሰራጭ አብራችሁ ያሉባልተኞችን ወሬ በመድገም ፋንታ «ከመሪዎቹ የተላከ መልእክት ባይሆን ኖሮ ተልኳል ብለው አይዋሹንም፣ ተቀብለነው አብረን እንሰራለን» በማለት ከመተማመን ውጭ ለችግራችን መፍቻ ሌላ ዘዴ ባልነበረበት ወቅት አመኔታ ሰጥታችሁን ከአለም አቀፉ አመራሩ ጋር ለመስራት በመቻላችሁ ከፍተኛ ምስጋናየን አቀርባሉ::

በግሌ፡ በእዚህ አዳራሽ ውስጥ ስንቶቻችሁን አመስግኜ እንደምጨርስ አላውቅም:: በተመሳሳይም በመላው አለም ለሚገኙ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶችንና አባላቶቻቸውን ላልተቆጠበ ድጋፋቸው አመሰግናለሁ:: « የቅንጅትን እንቅስቃሴ በዴሞክራሲ ላይ የቆመ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ቤት እንዲሆን ካላችሁ እምነት በመነሳት የድጋፍ ድርጅቶቻቸወሁን በማዋቀሩ ስራ ላይ እንድሳተፍ ከግል ኪሳችሁ ሳይቀር ወጪዎችን በመሸፈን፣ ከሀገር ሃገር ተንቀሳቅሼ ሃላፊነቴን እንድወጣ ላስቻላችሁኝ ወገኞቼ ምስጋናየን አቀርባለሁ:: ላሳያችሁኝ አመኔታ ፍቅርና ጨዋነት ከልቤ አመሰግናለሁ::

በስራቸው ባህርይ፣ በአካባቢያችን በምናያቸው ያልተገሩ ብእሮችና ምላሶች መሰደብ ባመፍራት የቅንጅት የድጋፍ ድርጅት አባላት ያልሆኑ ነገር ግን ቅንጅት ይዞት ለተነሳው ሃገራዊ ራእይ ቀና አስተያየት ላላቸው፣ ስማቸውንና ድምጻቸውን አጥፍተው ቅንጅትን በከፍተኛ እውቀታቸውና ገንዘባቸው የረዱትን፣ የሰጧቸውን ስራ ትንሽና ትልቅ ሳያማርጡ ለትገሉ አስተዋጽኦ ላደረጉ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ወገኖቼ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ::

የቅንጅትን ስራ በሙሉ ጊዜየና በሙሉ ልቤ እንድሰራ በገንዘብ በቁሳቁስ ሞራልን የሚገናባ ምክር በመስጠት ለደገፉኝ ቤተሰቦቼ፣ ከቤተሰቦቼ ያላነሰ ተመሳሳይ ደግነትና ቸርነት ላሳዩኝ በመላው አለም ተበትነው ለሚኖሩ ወገኖቼ የከበረ ምስጋናየን አቀርባለሁ::

በመጨረሻም የቅንጅት የድጋፍ ድርጅት ሁሉን ያሳተፈ፣ ሁሉን ያቀፈ ዴሞክሲያዊ አደረጃጀት እንዲኖራቸው የሚለውን ሃሳብ በመቀበል ቅንጅትን አግዛለሁ እደግፋለሁ ያለውን በሙሉ በአንድ ጥላ በማሰባሰብ የመጀመሪያውን እርምጃ በድፍረት በመውሰድ ፋና ወጊ የሆነውን በታላቂቷ ብሪታንያ የሚገኘውን የቅንጅት የድጋፍ ድርጅት ለማመስገን እፈልጋለሁ:: የእዚህ አደረጃጀት ሃሳብ በአንግሊዝ ሃገር በሚገኙ የቅንጅት ደጋፊዎች ተቀባይነት ባያገኝ ኖሮ በሌሎች ሃገሮች ይህንን ሃሳብ ተቀባይነት እንዲያገኝ በግሌ ያደረግሁት ጥረት ይሳካ ነበር የሚል እምነት የለኝም:: ይህ ብቻ አይደለም

የድጋፍ ድርጅቱ አባላት  ስራዬ የተሳካ እንዲሆን በጋራና በግል ያደረጉልኝ የሞራል የገንዘብ የምክር ድጋፍ ዘርዝሬ አልጨርሰውም። ያለእናንተ ደጀንነት የለእናንተ ጋሻና መከታነት የፊት የፊቱን እያሰብኩ በመራመድ የተሰጠንኝ አደራ ፈጽሜ አደራውን ለሰጡኝ መሪዎቻችን ማስረከብ ያስቸግረኝ ነበር።

ትልቅ ምስጋና ለእንግሊዝ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅት።

ምስጋና ለሁላችሁም

ምስጋና ለቅንጅት ሲሉ ትልቅም ይሁን ትንሽ ባቅማቸው ትግሉን ለደገፉ በሙሉ።

ያለ ትግል የዴሞክራሲና የነጻነት ባለቤት መሆን አንችልም! !
በቅንጀት ጥላ ስር ታግለን ማሸነፋችን ግን አይቀርም ! !